ከተማና መሠረት ልማት ሚኒስቴር

Ministry of Urban and Infrastructure

## በከተሞች ምግብ ዋስትናና ሴፍቲኔት ጽ/ቤት

# በኦሮሚያ ብ/ክ/መ የሁለተኛው ምዕራፍ የምግብ ዋስትናና ሴፍቲኔት እና ሥራ ፕሮጀክት የአካባቢ ልማት ሥራዎች ፋይዳ የዳሰሳ ጥናት


ዋና አዘጋጅ፡ **በዘርይሁን ተፃፈ**

በጥናቱ ወቅት የመስክ ደጋፊ አባላት

1. ሙሉጌታ ታመነ
2. መሐመድ ከተማ
3. አንማው እንደገና
4. እዮብ ማሞ (ሾፌር)


**ሪፖርት**

**ለአቶ ብርሃኑ ተሸመ (የከ/ም/ዋ/ሴ/ጽ/ቤት ኃላፊ)**

**ሚያዚያ፡ 2016 ዓ/ም**

**ከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር**

**ማውጫ** **ገጽ**


1.1 መግቢያ ........ 1

1.2 ዓላማ ........ 2

1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 2

1.4 የጥናቱ ወሰን ........ 2

1.5 የጥናቱ ውስንነት ........ 3

1.6 የጥናቱ ዘዴ ........ 3

1.7 የጥናቱ ናሙና አወሳሰድ ስልት ........ 4

1.8 የጥናቱ መረጃ ትንተና ዘዴ ........ 4

ክፍል ሁለት ........ 5

የተዛማጅ ፁሑፎች ዳሰሳ ........ 5

2.1. የከተሞች የአካባቢ ልማት ሥራዎች ጥቅሞች ........ 5

ክፍል ሦስት ........ 11

3.በጥናቱ የተሳተፉ ተጠቃሚዎችና የብረተሰብ ክፍሎች ማህበራዊ ማንነት ምግለጫ ........ 11

3.1. በጥናቱ የተሳተፉ የተጠቃሚዎች መግለጫ ........ 11

3.2. በጥናቱ የተሳተፉ የህብረተሰብ ክፍሎች መግለጫ ........ 12

ክፍል አራት ........ 16

4.የጥናቱ ግንቶች ........ 16

4.የUPSNJP የምግብ ዋስትናና ሴፍቲኔት ፕሮጀክት የአካባቢ ልማት ሥራዎች ፋይዳዎች ........ 16

4.1. የተጠቃሚዎች በአካባቢ ልማት ተሳትፎ ........ 16

4.2. የአካባቢ ልማት ሥራዎች ሳይቶች ምርጫ ........ 17

4.3. የአካባቢ ትማት ተግባራት አጠቃልይ ድምር ውጤቶች ........ 17

4.4. የአካባቢ ልማት ሥራዎች ጠቀሜታ ........ 23

4.5 የአካባቢ ልማት ሥራዎች ፍይዳዎች ........ 24

I. ማህበራዊ ፋይዳዎች ........ 24

II. ኢኮኖሚያዊ ፋዳዎች ........ 29

III. አካባቢያዊ ፋይዳዎች ........ 31

4.6. መሻሻል እና መሟላት ያለባቸው ጉዳዮች ........ 34

ክፍል አምስት ........................................................................................................................................................36
5. ማጠቃለያና ምክረሃሳብ..................................................................................................................................................36
5.1.ማጠቃለያ ...............................................................................................................................................36
5.2. ምክረሃሳብ ...........................................................................................................................................36
ማጠቀሻዎች ..............................................................................................................................................................37

## ክፍል አንድ

### 1.1 መግቢያ

የኢትዮጵያ የከተሞች ማህበራዊ ዋስትና ፖሊሲ ተፈጻሚ ለማድረግ የከተሞች የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ በሀገር አቀፍ ደረጃ ተቀርጾ  በመንግስትና በዓለም ባንክ ትብብር ከ2009 ዓ.ም ጀምሮ የከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞ ተግባራዊ በመሆኑ በከተሞች ለተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ችግሮች ተጋላጭ የሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎችን ሰርቶ የማግኘትና ጥሪት የመያዝ አቅምን በማጎልበት የስራ ዕድልን በመፍጠር የኑሮ ሁኔታን የማሻሻል ድጋፍ እንዲያገኙ የማድረግና ዜጎች ለከፋ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ችግሮች እንዳይጋለጡ የመከላከል ሥራ በፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ከተሞች ውጤት እያስገኘ መጥቷል፡፡

የከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮጀክት በከተሞች ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን ገቢያቸውን በማሻሻል በከተሞች የተንሰራፋውን ድህነት ለመቀነስ ዓላማ ያደረገው የከተማ ልማታዊ ሴፍቲኔትና ሥራ ፕሮጀክት በመጀመሪያ በ2011 ዓ.ም በአስራ አንድ (11) ዋና ዋና ከተሞች ተጀምሮ በ2014 የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ ከተሞችን ቁጥር ወደ ሰማንያ ስምንት (88) በማሳደግ የአካባቢ ልማት ስራዎች በጵሮጀክቱ እየተከናወኑ ይገኛል፡፡ በከተማ የሚስተዋለውን የዜጎች የምግብ ዋስትና ችግር ለመቅረፍ ዜጎችን በማህበረሰብ አቀፍ የአካባቢ ልማት ስራዎች በዋናነት በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፣ በአረንጓዴ ልማት፣ በተፋሰስ ልማት፣ አነስተኛመሰረተ ልማት ስራዎች እንዲሁም ለከተማ ግብርና ምቹ ሁኔታ መፍጠር ላይ በማሳተፍ የምግብ ዋስትናቸውን እንዲያረጋጡ ዘርፈ ብዙ ስራዎች ተግባራዊ በመደረግ ላይ ይገኛል፡፡

ስለሆነም በከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮጀክት የአካባቢ ልማት ስራዎችን አጠናክሮ ለመቀጠል የሚታዩ ጉድለቶችን በዘላቂነት ለመፍታት፣ የልማት ስራዎች ያመጣውን አዎንታዊ ስኬቶችን ለማስፋት፣ የኅብረተሰቡንና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎ በማጠናከር በየጊዜው የሚነሱ የህብረተሰቡን ጥያቄዎችን መሰረት ያደረገ ዘላቂ መፍትሄ በመፈለግ እንዲሁም የአካባቢ ልማት ስራዎች ለከተሞች ውብ ገጽታ የሚያበረክተውን አስተዋጽኦ ለማሳደግና በዘርፉ የሚታየውን የማስፈጸም አቅም ውስንነት ለመፍታት የሚያስችል ዘርፈ ብዙ ስራዎችን መስራት አስፈላጊ ነው፡፡ ለዚህም በከተሞች ምግብ ዋስትናና ሴፍቲኔት ፕሮጀክት የተሰሩ የአካባቢ ልማት ስራዎች በአካባቢ እና ማህበረሰብ ላይ የሚያሳድረው የተጽዕኖ ደረጃ የሚያሳይ የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ አስፈላጊ በመሆኑ  በኦሮሚያ ብ/ክ/መ/ ናሙና ከተሞችን መሠረት በማድረግ ይህ መነሻ የዳሰሳ ጥናት ተካሂዷል፡፡

## 1.2 ዓላማ

ጥቅል ዓላማ

- የጥናቱ ዋና ዓላማ በከተሞች ምግብ ዋስትናና ሴፍቲኔት ፕሮጀክት የተሰሩ የአካባቢ ልማት ስራዎች ለተጠቃሚው፣ ለህብረተሰቡና ለተፈጥሮ አካባቢ ያስገኛቸውን ጥቅሞች ለመዳሰስ ነው፡፡

**ዝርዝር ዓላማዎች**

- በአካባቢ ልማት ስራዎች የተገኙ መልካም አጋጣሚዎችንና ተግዳሮቶችን መለየት፣
- በከተሞች የምግብ ዋስትናና ሴፍቲኔት ፕሮጀክት የተሰሩ የአካባቢ ልማት ስራዎችን ስገኙአቸው ውጤቶን መለየት፣
- የተሰሩ የአካባቢ ልማት ስራዎች በአካባቢ እና ማህበረሰብ ላይ ያመጣውን አዎንታዊ ለውጥ መለየት፣
- በአካባቢ ልማት ስራዎችን፣ የህብረተሰቡን ተሳታፊነትን፣ ባለቤትነትንና ተጠቃሚነትን ሊያጎለብቱ በሚችሉ ጉዳዮች ላይ ምክረ-ሃሳብ ማቅረብ፣

## 1.3 የጥናቱ አስፈላጊነት

ከዚህ በፊት በከተሞች የምግብ ዋስትናና ሴፍቲኔት ስራ ፕሮጀክት የለሙ የአካባቢ ልማት ሥራዎች በአካባቢ እና ማህበረሰብ ላይ ያመጡትን ለውጥ የሚያሳይ ጥናት ከለመኖሩ የተነሳ በዘርፉ  የሚሰሩ ስራዎች በተፈጥሮ አካባቢ እና ማህበረሰብ ላይ ስለሚያመጡት አሉታዊና አዎንታዊ ተጽዕኖ እና የማሻሻያ አማራጭ የመፍትሄ ምክረ-ሀሳብ ለመጠቆም የሚያስችል የዳሰሳ ጥናት ማካሄድ አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በተጨማሪ ይህ ጥናት በከተሞች ምግብ ዋስትናና ሴፍቲኔት ስራ ፕሮጀክት የለሙ የአካባቢ ልማት ሥራዎች በአካባቢ እና ማህበረሰብ ላይ ባመጣው አዎንታዊ ለውጥ ላይ የውሳኔ ሀሳብና የፖሊሲ መነሻ ለሚሹ አካላት የመነሻ ሀሳብ ለማቅረብ እና በጉዳዩ ላይ በስፋትና በጥልቀት ለሚያጠኑ አካላት የመነሻ ሀሳብ ግብዓት ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡

## 1.4 የጥናቱ ወሰን

በሀገር አቀፍ ደረጃ በከተሞች ምግብ ዋስትናና ሴፍቲኔት ፕሮጀክት የአካባቢ ልማት ስራዎች ተግባራት ዘርፈ ብዙ ጥናቶችን ማጥናት አስፈላጊ ቢሆንም ይህ ጥናት በዋናነት ያተኮረው በፕሮጀክቱ የተሰሩ የአካባቢ ልማት ሥራዎች በተፈጥሮ አካባቢ እና ማህበረሰብ ላይ ያመጠውን አዎንታዊ ለውጥ/ ፋይዳ መለየት ሲሆን ጥናት የጥናቱ በተመረጡ 5 ከተሞች ዴራ፣ አሰላ፣ ሮቤ፣ ባቱና ቢሾፍቱ ያካተተ ነው፡፡

### 1.5 የጥናቱ ውስንነት

ይህ የዳሰሳ ጥናት በፕሮጀክቱ የተሰሩ የአካባቢ ልማት ስራዎች ለህብተሰቡ እና ተፈጥሮ አካባቢ ባስገኘው አዎንታዊ ፋይዳዎች ላይ ብቻ ያተኮረ መሆኑ፣ በአካባቢ ልማት ስራዎች ስኬት፣ ተግዳሮትና ፋይዳውን በሚመለከት ተዛማጅ መነሻ ጥናቶች አለመኖሩ፣ የጥናቱ መረጃ ወሰን በጸጥታ ምክንያት የተወሰኑ ክልሎችን ያላካተተ መሆኑ እንዲሁም የመረጃ እጥረትና የጥናቱ ውስንነት ነው፡፡

### 1.6 የጥናቱ ዘዴ

ለመረጃ አሰባሰብ መነሻነት የጥናት ዘዴን ለመወሰን እንዲያስችል መረጃው እንዲኖረው የሚፈለገው የትክክለኛነት መጠን፤ የሚሰበሰበው የመረጃ አይነትና ጥልቀት፣ የመረጃ ምንጮች በናሙና ለመለየትና ለማግኘት የሚቻልበትን መንገድ ታሳቢ አድርጓል፡፡

ለጥናቱ የመጀመሪያና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮች (Primary and Secondary data) የሚሰበሰቡ የመረጃ አይነቶች አሀዛዊ (Quantitative) እና ሀተታዊ (Qualitative) ይሆናል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ መረጃዎችን በመጠይቅ፣ በቃለ-መጠይቅ፣ ቡድን ውይይት እና በመስክ ምልከታ የሚሰበሰብ ሲሆን መጠይቆች መረጃ ሰጪው የሚፅፍበት ክፍት መጠይቅ (open-ended) ወይንም አማራጮች ቀርበውለት የሚመርጥበትን ክፍት ያልሆነ (close ended) ሂደቶችን ተካተዋል፡፡

የሁለተኛ ደረጃ መረጃ ምንጮች ደግሞ በመንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ አካላት ታትመው ወይንም ሳይታተሙ የወጡ ሪፖርቶች/ ሰነዶች፣ መፅሐፍት፣ መፅሔቶች፣ ጥናታዊ ጽሁፎች እና ከኢንተርኔት የተገኙ ናቸው፡፡

በዘርፉ የተዘጋጁ ጽሁፎችን በመዳሰስ፣ በተዘጋጀው መጠይቅ መሰረት መረጃ በመሰብሰብ፣ ከሚመለከታቸው የመንግስት ተቋማት፣ ከባለድርሻ አካላት፣ ፕሮጀክት ተጠቃሚዎች እና ከአከባቢ ማህበረሰብ ጋር ውይይት በማድረግ፣ የመስክ ምልከታ በማካሄድ፣ የተለያዩ ሪፖርቶች/ ሰነዶች፣ መፅሐፍት፣ መፅሔቶች፣ ጥናታዊ ጽሁፎች እና ከኢንተርኔት የተገኙ መረጃዎችን በመዳሰስ እንዲሁም ከሚመለከታቸው የስራ ክፍል ኃላፊዎችና ባለሙያዎችን በማካተት ተሰብስቧል፡፡


ለዳሰሳ ጥናቱ አስፈላጊ የሆኑ የመጀመሪያ ደረጃ መረጃ ምንጮች (የዘርፉ ያስራ ክፍል ኃላፊዎችና ባለሙያዎች፣ የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች፣ የአካባቢ ማህበረሰብ እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላት) በመጠቀም የተሰበሰበ ሲሆን የሁለተኛ ደረጃ መረጃ የተሰበሰበው በመንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ ባለድርሻ አካላት

ታትመው ወይንም ሳይታተሙ የወጡ ሪፖርቶች ወይም ሰነዶች፣ ቀጥተኛና ተዛማጅ ሰነዶችና ጽሑፎች፣ መፅሔቶች፣ ጥናታዊ ጽሁፎች፣ ፖሊሲዎችና ሌሎች ተዛማጅ መጣጥፎች ናቸው።

## 1.7 የጥናቱ ናሙና አወሳሰድ ስልት

ለዚህ ጥናት ከ88 ተጠቃሚ ከተሞች መካከል 15 ከተሞች በዓላማ ተኮር የናሙና አወሳሰድ ዘዴ (Purposive Sampling/ judgmental sampling) የተመረጡ ሲሆን ለናሙና መነሻ ምክንያት የከተሞች ጂኦግራፊያዊ መገኛ ቅርርቦሽ፣ በክልሎች የተጠቃሚ ከተሞች ብዛት እንዲሁም በአንጻሩ አስተማማኝ ሰላምና ጸጥታ ያሉባቸው ከተሞች ለጥናት መሰረታዊ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተመርጠዋል።

ለጥናቱ ናሙና ከተለየው ወይም ከተመረጠው ጠቅላላ ናሙና ብዛት 17% ከሚሆኑት ላይ መረጃ ቢወሰድ በቂ መሆኑን (Rule of Thumb) ከተምብ መመሪያ (L. R. Gay,1987) ያረጋገጠ በመሆኑ ከጠቅላላ ናሙና ብዛት (17%) አስር በመቶ ከሚሆኑት አስፈላጊ መረጃዎች ተሰብስበዋል።




## 1.8 የጥናቱ መረጃ ትንተና ዘዴ

ለጥናት የተሰበሰሰቡ መረጃዎች በአሀዛዊ (Quantitative) እና ሀተታዊ (Qualitative) ዘዴ ተንትነዋል። በአሀዛዊ (Quantitative) የተነተኑት መረጃዎች የተገለፁት በሰንጠረዥ፣ በፐርሰንት፣ በግራፍ እና ምስልን በመጠቀም ሲሆን በሀተታዊ (Qualitative) መንገድ የሚተነተኑ መረጃዎች የተገለፁት በፅሁፍ ትንተና ሲሆን ቀላል የሆኑ ስታትስቲካዊ ዘዴዎች ከጥናቱ የሚገኙ መረጃዎችን ለመተንተንና ለመተንበይ ስለሚያስችል ተግባራዊ ሆነዋል።

## ክፍል ሁለት

## የተዛማጅ ፁሑፎች ዳሰሳ

### 2.1. የከተሞች የአካባቢ ልማት ሥራዎች ጥቅሞች

በከተሞች የምግብ ዋስትናና ሴፍቲኔት ፕሮጀክት ከሚተገበሩ የአካባቢ ልማት ሥራዎች ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ተግባራት ማለትም የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና ማስወገድ፣ አረንጓዴ ልማት፣ የተፋሰስ ልማት፣ ከተማ ግብርና እና ተያያዥ የአነስተኛ መሠረተ ልማት ሥራዎች የተለያዩ ጥቅሞች ሲኖራቸው በዋናናነት እርስ በርስ ቁርኝት ያላቸው በኢኮኖሚያዊ፣ በማህበራዊእና አካባቢያዊ ያላቸው ጥቅሞች በአራት ዋና ዋና ሃሳቦች ተከፍሎ በዘርፉ የተዳሰሱ የተለያዩ ጥናቶች አብራርተዋል፡፡

1. **የምግብ ዋስትና የማረጋገጥና የጤና ጥቅሞች፦**

የከተሞች የምግብ ዋስትና የአካባቢ ልማት ሥራዎች በቀጥታ በወርሃዊ ክፍያና ባላቸው የሥራ ውጤቶች የተጠቃሚውን የምግብ ዋስትና በማረጋገጥ ለድሃውን የከተማ ህዝብ የተመጣጠነ እና የተሟላ የምግብ አቅርቦት እንዲኖረው በማድረግ ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል፡፡ እጅግ በጣም ውድ የሆኑ የምግብ አይነቶች ለምሳሌ ፍራፍሬዎች፣ የጓሮ አትክልቶች፣ ስጋና የመሳሰሉትን በምግባቸው ውስጥ በቤት ምርታቸው እንዲያካትቱ በማስቻል ቤተሰቡ የተመጣጠነ ምግብ በማግኘት በምግብ እጥረት ምክንያት ከሚከሰቱ ችግሮች እንዲጠበቁ ያደርጋቸዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪም የከተማው ነዋሪ ትኩስ ያልተበላሹ የግብርና ምርት ውጤቶችን ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማስቻል ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል፡፡

ከዚህ ሀሳብ ጋር በተገናኘ የዘርፉ አጥኚዎች በፕሮጀክቱ የሚተገበሩ የአካባቢ ልማት ሥራዎች በዘርፉ ለሚሳተፉ ተጠቃሚዎች በቀጥታ ርሀብና የምግብ እጥረትን በማስወገድ፣ የከተማው ድሃ ህብረተሰብ ጤነኛ፣ አምራች እና በሽታን የሚቋቋሙ ዜጎች እንዲሆኑ ያደርጋል በማለት ያብራራሉ፡፡ ከዚህ በተጨማሪም በከተማው የውሃ ብክለትንና በሽታ አምጪ የሆኑ ህዋሳትን በመቀነስ እና የአካባቢው ቆሻሻዎች በተሸለ መንገድ በመያዝ ዳግም ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ ከተሞች ንፁህ እና ውብ እንዲሆኑ ያደርጋል (Smit et al, 1996: 160)፡፡

የአካባቢ ልማት ሥራዎች በከተሞች የምግብ አቅርቦት መጠንን ከፍ በማድረግና ርሀብን በመቀነስ እና የምግብ ጥራትን በማሻሻል ዘርፉ ከፍተኛ ሚና የሚጫወት ሲሆን በተለይም በከተማ ግብርና ዘርፉ በተለያዩ ትልልቅ ከተሞች የምግብን ዋስትናን በማረጋገጥ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት የተለያዩ ጥናቶች ያብራራሉ፡፡

ከዚህ በተገናኘ በከተሞች በተካሄደው ጥናት ከተሞች የሚተገበሩ የከተማ ግብርና የአካባቢ ልማት ለምሳሌ የጓሮ አትክልት ምርት፣ በዶሮ እና በከብት እርባታ ራሳቸውን ችለው ህዝባቸውን መመገብ የሚያስችል መሆኑ

ተረጋግጧል። ለምሳሌ ዳካር የሀገሪቱን 60% የጓሮ አትክልት ፍጆታ እና 65-70% የዶሮ እርባታ ፍጆታ ትሸፍናለች (Mbaye etal; in Klemsu; 2000: 104)። እንደዚሁም ደግሞ 90% የጓሮ አትክልት ፍጆታ በራሷ በከተማዋ እንደሚሸፈን ጥናቶች ያሳያሉ (CENCOSAD 1994 in Klemsu;2000)። በዳሬሰላም ከ90% በላይ የሚሆነው ቅጠላቅጠል የጓሮ አትክልት የሚመረተው በከተማ ውስጥ ባሉ ባዶ ቦታዎችና በቤቶች ጓሮ እንደሆነ ተመሳሳይ ጥናቶች ያመለክታሉ (Stevenson et al 1996 in Klemsu; 2000: 104)። በሌላ በኩል በሀራሬ በከተማ ግብርና ላይ የተሰማራውን ህዝብ ቤተሰብ ተዘውታሪ ምግብ የአራት ወራት ከዘርፉ እንደሚሸፍንላቸው አንድ ጥናት ያመለክታል (Mbiba B., 2000)።

## 2. የገቢ ምንጭና የሥራ ዕድልን በመፍጠር ያለው ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች

የከተሞች የምግብ ዋስትና የአካባቢ ልማት ሥራዎች ለገቢ ምንጭነት፣ ከሥራ ምንጭነት፣ ከአነስተኛ የንግድ ተቋም ልማትና ከከተማ የምግብ አቅርቦት እና የከተማ ቦታ አጠቃቀም አንፃር ከሚኖራቸው ሚናዎች ሊታዩ ይችላሉ።

### ሀ. የሥራ ዕድል ፈጠራና የገቢ ምንጭ፣

የከተሞች የአካባቢ ልማት ሥራዎች ለሚሊዮኖች መኖሪያ ሆነው በከተማ ውስጥ እና በከተማ አካባቢ የሚተገበር አነስተኛ የሥራ ዘርፍ ነው። እንደ የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም አገላለፅ ዘርፉ አነስተኛ ክህሎትና ካፒታል ላላቸው እንዲሁም ሴቶች እና በእድሜ ለገፉ አዛውንት የከተማ ነዋሪዎች የገቢ ምንጭ በመሆን ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል (UNDP; 1996: 168)። በጥሬ ገንዘብ መጠነኛ ገቢን ማግኘት መቻል የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ከሚያስችሉ ጉዳዮች መሠረታዊ ነገሮች አንዱ ነው። ከሳሃራ በታች ባሉ አገሮች ከሚኖሩ የከተማ ነዋሪዎች በተለያዩ የሥራ ዘርፍ ተሰማርተው መደበኛ ደሞዝ ተከፍሎአቸው የሚተዳደሩ የሠራተኛው መጠን ከ10% በታች ነው (UNDP, 1996)። በመሆኑም ለከተማ ነዋሪዎች በትንሹም ቢሆን በትልቁ፣ በመደበኛም ሆነ በኢመደበኛ መንገድ በተለይም በታዳጊ አገሮች የከተማ ድሆች ተፎካካሪና በቂ ገቢን ከዘርፉ እያገኙ የዘርፉ ተጠቃሚዎች በመሆን የመኖር ዋስትናቸውን እንዲያረጋግጡ አስችሎአቸዋል።

አሁን በዘመናችን በዘርፍ ላይ የተካሄዱ አብዛኛዎች ጥናቶች አጽንኦት ሰጥተው የሚገልጹት ሥራውን ለመጀመር ቀላል መሆኑን ነው። ይህም የሆነበት ምክንያት በትንሽ መሬት፣ በትንሽ ወጪ እና በትንሽ ክህሎት ሥራውን መጀመር የሚቻል በመሆኑ ነው። ለምሳሌ በሉሳካ በሌላ ተሰማርቶ ሥራን ለመምራት ዕድሉ ለሌላቸው ምንም ችሎታና አቅም ለሌላቸው ለሴቶች፣ ለአዛውንቶች እና ለህፃናት በከተማ አካባቢ ልማትና ጥበቃ የሥራ ዕድልን በመፍጠር ከሌሎች መደበኛ ካልሆኑ የሥራ ዘርፎች ይልቅ ከፍተኛ ጥቅም በማግኘት ላይ ይገኛሉ (Sanyal, 1985 cited in UNDP, 1996: 172)። ምንም እንኳ በዚህ ደረጃ ከሥራው የሚገኘው

ውጤት አነስተኛ ቢሆንም በዘርፉ የሚሠማሩ የሥራ ተቋማት ደረጃ በደረጃ ዕውቀታቸውንና ክህሎታቸውን በማሳደግ ተጠቃሚነታቸውን በጥረት ማሳደግ እና ማስፋት እንደሚችሉ የሌሎች ከተሞች ተሞክሮ ያሳያል፡፡

**ለ. የምግብ አቅርቦትና ወጤታማ የከተማ መሬት አጠቃቀም**

የከተማ የአካባቢ ልማት ሥራ ለነዋሪው በግል እና በቡድን በቤተሰብ ከሚሰጠው ጥቅም ባሻገር ለሀገራዊ የኢኮኖሚ እድገትም አስተዋጽኦ አለው ተብሎ ይታመናል፡፡ ለዚሁም ምክንያቱ የከተማ ግብርና አን የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት የከተማው ህዝብ መሠረታዊ የምግብ ፍላጎትን በተለይም በጓሮ አተክልት በማርካት የከተሞችን የኢኮኖሚ አቅም በማጠናከር የብሄራዊውን የኢኮኖሚ እድገት ይደግፋል (Smit; 1996: 163)፡፡ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት በተለይም በትንሽ ገቢ ባላቸው ታዳጊ አገሮች የከተማ ግብርና እና የአካባቢ ልማት ለከተማው ህዝብ አንዱ የምግብ አቅራቢ ሀይል ነው ብለው ያስረዳሉ፡፡ ምክንያቱም ይህ በገጠር የማይመረቱትን ረዘም ባለ ጉዞ ውስጥ በቀላሉ የሚበላሹ የግብርና ውጤቶችን በማንኛውም ወቅት የሚያቀርብ በመሆኑ ነው፡፡ ስለዚህ ለብሔራዊው ጠቀሜታ እንደ ገጠሩ ግብርና ሁሉ መሠረታዊ እንጂ እንደ ተጨማሪ የምግብ አቅራቢ ሆኖ የሚታይ መሆን የለበትም፡፡

በሌላ በኩል እንደ የተባበሩት መንግስታት የልማት ፕሮግራም እይታ የከተማ የአካባቢ ልማት አዋጪና የመሬት ተጠቃሚነትን ከሚያረጋግጡ ዘርፎች አንዱ ነው፡፡ ድርጅቱ ይህንን ካለበት ምክንያቶች ከብዙ በጥቂቱ የሚከተሉት ይገኙባቸዋል (UNDP, 1996: 177-178)፡፡

- ለጊዜው ነፃ ሆነው የተቀመጡ መሬቶችንና በከተማ ማስፋፊያ ዞኖች አካባቢ ያሉትን ባዶ መሬቶችን ጥቅም ላይ በማዋል የገቢ ምንጭ አፍላቂ በመሆኑ፣
- ጥቅም ላይ ያልዋሉ የውሃ አካላትን እና ተዳፋታማ ሥፍራዎችን ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ የአፈሩን ለምነት መጠበቅ የሚያስችል በመሆኑ፣
- በተለያዩ ተቋማት የተያዙ ለግንባታ ያልዋሉ መሬቶችን ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ ገቢ የሚያስገኝ በመሆኑ፣
- ፓርኮችን፣ የስፖርት ሜዳዎችን፣ የዩኒቨርሲቲ ጊቢዎችን፣ የመንገድ ዳርቻዎችን፣ የወንዞች ዳርቻዎችን፣ ዘላቂ ማረፊያዎችን እና ሌሎች የከተማ አካባቢዎች ባዶ መሬቶችን በአግባቡ ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር አጣጥሞ መጠቀም የሚያስችል በመሆኑ፣
- የከተማ ዳርቻዎችን ለዶሮ እርባታ፣ ለጓሮ አትክልትና ለመሳሰሉት በማዋል የከተማ መሬትን በአግባቡ መጠቀም የሚያስችል በመሆኑ፣
- አብዛኛው የከተማ ግብርና ትንሽ መሬትን እና ዕውቀትን የሚፈልግ ቢሆንም ነገር ግን ለብዙዎች የሥራ ዕድል የሚፈጥር በመሆኑ፣ እና

- የከተማ ግብርና ለህዝብ አገልግሎት በሚውሉ ነገሮች ላይ የሚወጡ ወጪዎችን የሚቀንስ በመሆኑ ናቸው።

### 3. ለዘላቂ የከተሞች ዕድገት ያለው ጥቅም

የከተሞችን ቆሻሻ አያያዝ እና የሀብት አጠቃቀምን በአግባቡ እንዲመራ በማድረግ የአካባቢውን ደህንነት በማሻሻል ለከተሞች ዘላቂ ዕድገት ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል።

### ሀ. የከተሞችን አካባቢ ልማትና ደህንነት በማስጠበቅ

በዓለማችን በተለይም በታዳጊ አገሮች በከተሞች በሚታየው ከፍተኛ የህዝብ ቁጥር ዕድገት እና ተገቢ ያልሆነ ከቁጥጥር ውጭ የሆነ የመሬት አጠቃቀም እየጎዱት ያለው የከተማውን የውስጥ የተፈጥሮ አካባቢ ብቻ ሳይሆን በዙሪያው ያለውን ሥነ ምህዳር ጭምር ነው። ከላይ  የተገለፁት ተገቢ ያልሆኑ ተግባራት የአየር ብክለት፣ የውሃ ብክለት፣ የአካባቢው ሙቀት መጨመር፣ የአፈር መሸርሸር፣ የዕፅዋት ዝርያ መመናመን፣ የተፈጥሮ አደጋዎች ለምሳሌ ጎርፍና የመሳሰሉት መጨመርን ያስከትላሉ። የከተማ ግብርና የሚጫወተው ሚና እነዚህን ትልልቅ የከተማ ችግሮች በማስወገድ ብቻ ሳይሆን የአካባቢውን የተፈጥሮ ሚዛን እንዲጠበቅ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል።

ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር የአካባቢ ልማት እና የጥበቃ ሥራ በአመራሩና በከተማ ፕላን ዝግጅት ውስጥ ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶት ከታቀደ በከተማ ውስጥ የሚተከሉ የአትክልትና ደን ዛፎች ለአካባቢው የአየር እርጥበትን በመጨመር፣ ሙቀትን በመቀነስ እና መልካም መአዛን በመስጠት በካይ ጋዞችን በመቀነስ፣ የፀሐይ ብርሀንን በመቀበል ጥላ በመፍጠር እና ጠንካራ የነፋስ ሃይልን በመገደብ ከተሞች ለኑሮ ተስማሚ አካባቢ እንዲሆኑ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ በማለት በጥናታቸው አረጋግጠዋል (Deelstra, 2000: 22)።

### ለ. ለሳይንሳዊ የከተማ መሬት አጠቃቀምና አካባቢዎች ውበት

ከተሞች ዝቅተኛ ገቢ ባላቸው ህብረተሰብ አካባቢ ያሉት ባዶ ቦታዎች ለምሳሌ የመንገድ ዳርቻዎች፣ የወንዝ ዳርቻዎች፣ ለልዩ ልዩ መሠረተ-ልማት የዋሉ መሬት ዳርቻዎች ብዙውን ጊዜ ቆሻሻማና አስቀያሚ ቦታዎች ናቸው። ስለዚህ የከተማ የአካባቢ ጥበቃ ሥራ እነዚህን ቦታዎች በማፅዳትና በተገቢው መንገድ ሥራ ላይ እንዲውሉ በማድረግ፣ ለምግብ ምርት እና ለአረንጓዴ መሠረተ ልማት  መሬቶችን  ጥቅም ላይ በማዋል በዝቅተኛ ማዘጋጃ ቤት ወጪ የከተሞችን አካባቢዎች ውበት እንዲጠበቁ በማድረግ ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል (UNDP, 1996: 184)።

### ሐ. ለከተሞች ቆሻሻ አያያዝ ያለው ጥቅም

በዚህ ዘመን አብዛኛው ትልልቅ ከተሞች የአየር እና የውሃ ብክለት አምጪ ቆሻሻዎችን በአግባቡ በማስተዳደር በኩል ከፍተኛ ችግር እያጋጠማቸው ነው፡፡ ደረቅ ቆሻሻ እና ፍሳሽ ቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቦታዎችን ማዘጋጀት ለከተማ ማዘጋጃ ቤቶች ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቅ በመሆኑ የሰፊ በከተማ ህገወጥ የቆሻሻ መጣያ ቦታዎችን በማብዛት የተዘጋጀ ህጋዊ የቆሻሻ መጣያ በፍጥነት በቆሻሻ የሚሞሉ በመሆናቸው ማዘጋጃ ቤቶች የከተማን ክልል ሙሉ በሙሉ አገልግሎት ለመስጠት አቅም የላቸውም (UNDP, 1996: 186)፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ በመንገድ ዳር የሚከማቹ ቆሻሻዎች የአየር ብክለትና የጤና ቀውስ በማስከተል ከፍተኛ ጉዳት በማስከተል ላይ ናቸው፡፡ ስለዚህ እንደ ጃክ እና ሌሎች አመለካከት ለዘላቂ የከተሞች ደህንነት ለማስጠበቅ ከተሞች በቆሻሻ አያያዝ እና አጠቃቀም ዙሪያ የቴክኖሎጂ ሽግግር በማድረግ ደረቅ ቆሻሻዎች ለእርሻ እና ለከብቶች መኖ እንዲሁም ቆሻሻ ውሃዎች ተጣርተው በመስኖ ወይም በቀጥታ ለፍራፍሬ ዛፍ ምርት እንዲውሉ ማድረግ ያስፈልጋቸዋል (Smit; 1996: 196)፡፡

### መ. ለተፈጥሮ ሐብት ጥበቃና ለአደጋ መከላከል ያለው ጥቅም

የከተማ ግብርና በምትክ የኃይል አቅርቦት አማራጭ በመሆኑ ለማገዶና ለተለያዩ ጉዳዮች በሚኖረው የደን መጨፍጨፍ ምክንያት በተፈጥሮ ደን ላይ ያለውን ጫና በመቀነስ በተፈጥሮ ሐብት ላይ የሚደርሰውን ውድመት በመከላከል ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል፡፡ የከተማ ግብርና የከተማ ቦታዎችን እና የፍሳሽ ውሃዎች ያለብክነት በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ ለቆጣቢ የመሬትና የውሃ ሀብት አጠቃቀም መሳሪያ ነው (Sachs and Silk; 1990 in UNDP; 1996: 189)፡፡

የከተማ የአካባቢ ልማት ሥራዎች ለተፈጥሮ አደጋ የተጋለጡ የከተማ አካባቢዎች ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን እንዲቀንሱ በማድረግ የበኩሉን ሚና ይጫወታል፡፡ ለምሳሌ ተራራማ አካባቢዎች እና የወንዝ ዳርቻዎች በማልማት በነፋስና በውሃ ምክንያት የሚደርሱ ጉዳቶችን መቀነስ ይቻላል፡፡

### 4.ማህበራዊ ትቅሞች

የከተማ የአካባቢ ልማት ሥራዎች ለህብረተሰቡ የሥራ ዕድል በመፍጠርና በቀጥታ ተጠቃሚ በማድረግ በከተሞች በስፋት የሚስተዋሉ ማህበራዊ ቀውሶች ለምሳሌ ልመናን፣ ሴተኛ አዳሪነትን፣ ወንጀልና እና የመሳሰሉትን እንዲቀንሱ በማድረግና በመዋጋት ከፍተኛ ድርሻ እየተወጣ ይገኛል፡፡ በከተማ የሚተከሉ የአትክልትና የደን ዛፎች ህብረተሰቡ በልዩ ልዩ ምክንያቶች አብሮ ተሰባስቦ እነዲማከር ከማድረጉም በላይ

የከተማ መዝናኛ ፓርኮች የተለያዩ ማህበረሰብ ክፍሎች በቀጥሮ ተገኛኝተው ለመዝናናትና አብሮ ለመምከር ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ማህበራዊ ጥቅሞችን እየሰጠ በተግባር እየታዬ ይገኛል፡፡

ክፍል ሦስት

## 3.በጥናቱ የተሳተፉ ተጠቃሚዎችና የብረተሰብ ክፍሎች ማህበራዊ ማንነት ምግለጫ

### 3.1. በጥናቱ የተሳተፉ የተጠቃሚዎች መግለጫ

የአካባቢ ልማት ሥራዎች ፋይዳ ጥናት በዚህ በናሙና ከተሞች ሃምሳ ተጠቃሚዎች ተመርጠው ምላሽ የሰጡ ሲሆን የነዚህም የመላሽ ተሳታፊዎች እና የህብረተሰቡ ማንነት በሰንጠረዥ አንድ እና በሰንጠረዥ ሁለት ማጠቃለያው እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ1. የተጠቃሚዎች ማንነት መግለጫ ሰንጠረዥ

| 1 | የተጠያቂዎች አድራሻ ከተማ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ከተማ | ብዛት | % |
| | 1 | ጴራ | 10 | 20% |
| | 2 | አሰላ | 10 | 20% |
| | 3 | ሮቤ | 10 | 20% |
| | 4 | ባቱ | 10 | 20% |
| | 5 | ቢሾፍቱ | 10 | 20% |
| | | ድምር | 50 | 100% |

| 2 | የተጠያቂዎች ጾታ | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ጾታ | ጴራ | አሰላ | ሮቤ | ባቱ | ቢሾፍቱ | ድምር |
| | | ወ | 6 | 4 | 4 | 4 | 1 | 19 |
| | | ሴ | 4 | 6 | 6 | 6 | 9 | 31 |
| | | ድምር | 10 | 10 | 10 | 10 | 10 | 50 |

| 3 | የተጠያቂዎች ዕድሜ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከተማ | ጴራ | አሰላ | ሮቤ | ባቱ | ቢሾፍቱ | ድምር |
| | 1 | 19-35 | 2 | 2 | 6 | 4 | 5 | 19 |
| | 2 | 35-50 | 5 | 6 | 4 | 4 | 3 | 22 |
| | 3 | 50-60 | 3 | 2 | 0 | 2 | 2 | 9 |
| | 4 | ድምር | 10 | 10 | 10 | 10 | 10 | 50 |

| 4 | የተጠያቂዎች ቤተሰብ ብዛት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ቤተሰብ | ጴራ | አሰላ | ሮቤ | ባቱ | ቢሾፍቱ | ድምር |
| | | 4 | 8 | 9 | 9 | 6 | 10 | 42 |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | 3 | 2 | 1 | 1 | 3 | 0 | 7 |
| | | 2 | 0 | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 |
| | | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| | | ድምር | 10 | 10 | 10 | 10 | 10 | 50 |

| 5 | የተጠያቂዎች ኃላፊነት | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከተማ | ዴራ | አሰላ | ሮቤ | ባቱ | ቢሾፍቱ | ድምር |
| | 1 | አባወራ | 6 | 4 | 4 | 4 | 1 | 19 |
| | 2 | እማወራ | 4 | 6 | 6 | 6 | 9 | 31 |
| | 3 | ልጅ | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| | | ድምር | 10 | 10 | 10 | 10 | 10 | 50 |

| 6 | የተጠያቂዎች የትምህርት ደረጃ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከተማ | ዴራ | አሰላ | ሮቤ | ባቱ | ቢሾፍቱ | ድምር |
| | 1 | ማንበብ የማይችል | 6 | 4 | 0 | 2 | 0 | 12 |
| | 2 | ማንበብና መፃፍ የሚችል | 0 | 1 | 2 | 0 | 3 | 6 |
| | 3 | አንደኛ ደረጃ | 1 | 3 | 0 | 5 | 1 | 10 |
| | 4 | 2ኛ ደረጃ | 3 | 2 | 7 | 3 | 5 | 20 |
| | 5 | ቴክኒክና ሙያ | 0 | 0 | 1 | 0 | 1 | 2 |
| | | ከዛ በላይ | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| | | ድምር | 10 | 10 | 10 | 10 | 10 | 50 |

| 5 | የተጠያቂዎች በፕሮጀክቱ የቆታ ጊዜ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዴራ | አሰላ | ሮቤ | ባቱ | ቢሾፍቱ | ድምር |
| | 1 | 2 ዓመት | 10 | 8 | 8 | 0 | 5 | 31 |
| | 2 | 1 ዓመት | 0 | 2 | 2 | 10 | 5 | 19 |
| | | ድምር | 10 | 10 | 10 | 10 | 10 | 50 |

### 3.2. በጥናቱ የተሳተፉ የህብረተሰብ ክፍሎች መግለጫ

በምግብ ዋስትና የአካባቢ ልማት ሥራዎች ፋይዳ ጥናት በናሙናነት ከተመረጡ ከተሞች ሰላሳ የህብረተሰብ ክፍሎች ተመርጠው ምላሽ የሰጡ ሲሆን የነዚህም ተሳታፊዎች የህብረተሰብ ክፍሎች ማንነት በሰንጠረዥ በሰንጠረዥ ሁለት ዝርዝር እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

**ሰንጠረዥ2. የህብረተሰቡ ተወካዮች ማንነት መግለጫ ሰንጠረዥ**

| 1 | የተጠያቂዎች አድራሻ ከተማ | | | |
|---|---|---|---|---|
| | | ከተማ | ብዛት | % |
| | 1 | ዴራ | 6 | 20% |
| | 2 | አሰላ | 6 | 20% |
| | 3 | ሮቤ | 6 | 20% |
| | 4 | ባቱ | 6 | 20% |
| | 5 | ቢሾፍቱ | 6 | 20% |
| | | ድምር | 30 | 100% |


| 2 | የተጠያቂዎች ጾታ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ዴራ | አሰላ | ሮቤ | ባቱ | ቢሾፍቱ | ድምር |
| | 1 | ወ | 4 | 1 | 3 | 3 | 3 | 14 |
| | 2 | ሴ | 2 | 5 | 3 | 2 | 3 | 15 |
| | 3 | ድምር | 6 | 6 | 6 | 5 | 6 | 29 |


| 3 | የተጠያቂዎች ዕድሜ | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከተማ | ዴራ | አሰላ | ሮቤ | ባቱ | ቢሾፍቱ | ድምር |
| | 1 | 19-35 | 3 | 4 | 2 | 2 | 3 | 14 |
| | 2 | 35-50 | 2 | 2 | 4 | 3 | 2 | 13 |
| | 3 | 50-60 | 1 | 0 | 0 | 0 | 1 | 2 |
| | 4 | ድምር | 6 | 6 | 6 | 5 | 6 | 29 |


| 6 | የተጠያቂዎች የትምህርት ደረጃ | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ከተማ | ዴራ | አሰላ | ሮቤ | ባቱ | ቢሾፍቱ | ድምር | |
| | 1 | ማንበብ የማይችል | 1 | 0 | 1 | 0 | 0 | 2 | |
| | 2 | ማንበብና መፃፍ የሚችል | 0 | 0 | | 1 | 0 | 1 | |
| | 3 | አንደኛ ደረጃ | 4 | 2 | 1 | 0 | 0 | 7 | |
| | 4 | 2ኛ ደረጃ | 0 | 3 | 1 | 3 | 1 | 8 | |
| | 5 | ቴክኒክና ሙያ | 0 | 0 | 2 | 0 | 3 | 5 | |
| | | ከዛ በላይ | 1 | 1 | 1 | 1 | 2 | 6 | |
| | | ድምር | 6 | 6 | 6 | 5 | 6 | 29 | |


### 3.3. የምላሽ ተሳታፊዎች ማንነት ጠቅል መግለጫ


#### 3.3.1. የተጠያቂ ተጠቃሚዎች ማንነት በፆታ፣ በዕድሜ፣ በቤተሰብ ብዛት እና በትምህርት ደረጃ



የተጠያቂ ተጠቃሚዎች ማንነት በፆታ
ብዛት
100
50
0
ወ
ሴ
ድምር
ድምር 19 31 50
% 38% 62% 100%


የተጠያቂ ተጠቃሚዎች ማንነት በዕድሜ
ብዛት
60
50
40
30
20
10
0
19-35
35-50
50-60
ድምር
ድምር 19 22 9 50
% 38% 44% 18% 100%



ብዛት
60
40
20
0
ድምር
%



ተጠያቂ ተጠያቂዎች በቤተሰብ ብዛት
ብዛት
60
50
40
30
20
10
0
4
3
2
1
ድምር
ድምር 42 7 1 0 50
% 84% 14% 2% 0% 100%





3.2.2. ከህብረተሰቡ ምላሽ የሰጡ ማንነት በፆታ፣ በዕድሜ፣ እና በትምህርት ደረጃ







## ክፍል አራት

## 4.የጥናቱ ግንቶች

## 4.የUPSNJP የምግብ ዋስትናና ሴፍቲኔት ፕሮጀክት የአካባቢ ልማት ሥራዎች ፋይዳዎች


### 4.1. የተጠቃሚዎች በአካባቢ ልማት ተሳትፎ

የአካባቢ ልማት ተጠቃሚዎች በአብዛኛው የሥራ ዓይነቶች እንደሚሳተፉ በዚህ ጥናት ተለይቷል፡፡ በተለይም ከ90% በላይ የሆኑት በደረቅ ቆሻሻና በአረንጓዴ ልማት የሚሳተፉ መሆኑ ጥናቱ ለይቷል፡፡




### 4.2. የአካባቢ ልማት ሥራዎች ሳይቶች ምርጫ

በከተሞች ያሉ የአካባቢ ልማት ሳይቶች ምርጫ የሚከናወነው በህብረተሰቡ ተሳትፎ መሆኑ ሙሉበሙሉ የተጠቃሚዎች ምላሽ ጥናቱ ለይቷል፡፡




| | አው | አይደለም | ድምር |
|---|---|---|---|
| ድምር | 100 | 0 | 100 |
| % | 100% | 0% | 100% |

### 4.3. የአካባቢ ትማት ተግባራት አጠቃልይ ድምር ውጤቶች

ፕሮጀክቱ አቅዶ ከተነሳባቸው ዋና ዓላማዎች አንዱ በየአካባቢ ልማት ሥራን በከተሞች በማከናወን ዜጎችን ከአስከፊ ድህነት የማላቀቅና የምግብ ዋስትናን የማሻሻል ሥራን ማሳካት ነው፡፡ ስለሆነም ከኦሮሚያ ብ/ክ/መ ከተማ ልማትና ቤቶች ቢሮ የምግብ ዋስትና ጽ/ቤት 2016 ዓ.ም  በተገኘው መረጃ መሠረት በጥናቱ ናሙና 5 ከተሞች የአካባቢ ልማት ዋናዋና ተግባራት ድምር ውጤት ቀጥሎ ባለው ሰንጠረዥ የተመለከተ ሲሆን በዚህ ጥናት የሚከተለው ውጤት ተለይቷል፡፡

1. በደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ በጥናቱ 5 ናሙና ከተሞች በድምር 25,097,144.56 ኪ.ግ ደረቅ ቆሻሻ በመሰብሰብ ከተሞችን ጽዱ በማድረግ የህብረተሰቡን ጤንነት ማስጠበቅ ተችሏል፡፡

2. በከተማ ውበት እና አረንጓዴ ልማት 398,920 የቁጥቋጦ፣ 132,055.00 የትክልትና ፍራፍሬ፣ 425,378.00 የደን ዛፎች በከተሞች ተተክለው ዛፎች የሚሰጡትን ጥቅም ናሙና ከተሞች ማግኘታቸው ተሌቷል
3. በተፋሰስ ልማት 1 ኪ.ሜ የዕርከን ስራ፣ 4,456.00 ኪ.ሜ የድንጋይ ካብ፣ 5,543.00 የዛፍ ችግኝ ተከላ እና የመሳሰሉት ተከናውነው የአፈር ጥበቃ ሥራ በከተሞች ተከናውኖ የአፈር ጥበቃ ሥራ ተሰርቷል፡፡
4. ለከተማ ግብርና ምቹ ሁኔታን ከመፍጠር አንጻር ወደ 90 ሄክታር ቆሻሻ ቦታዎች ጽድተው ለግብርን ምቹ ሆነው ተዘጋጅተው ተጠቃሚዎች ተጨማሪ ገቢ እንዲገኙ አስችሏል፡፡
5. በአነስተኛ መሠረተ ልማት 3 የህዝብ ሽንት ቤት 2 የህጻናት ማቆያ ማዕከል፣ 6 የህጻናት ማቆያ ድንኳን፣ 3.8 ኪ.ሜ የመንገድ ጥገና የት/ ቤት ግንባታ እና በማህበራዊ ትስስር የተጠቃሚዎች የመኖሪያ ቤት እድሳት ተከናውኖ ከተሞች የፋይዳው ተጠቃሚ ሆነዋል

ሰንጠረዝ 3. የአካባቢ ልማት ሥራዎች ውጤቶች ሰንጠረዥ

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | Region Oromiya Regional State | | | | | | | |
| | UPSNJP 2022 -2024 cumulative Performance data interms of Major activities work load | | | | | | | |
| | City | | Dhera | Assela | Robe | Batu | Bishoftu | |
| RN | Category | Unit | work load Achieved | work load Achieved | work load Achieved | work load Achieved | work load Achieved | Total Sum |
| 1 | Urban solid waste &environmental cleaning | | | | | | | |
| | Road side cleaning (pedestrian walkway or internal roads) | Kg | 863,465.00 | 1371632 | 2349586 | 3048708 | 3973996.48 | **11,607,387.85** |
| | cleaning market and public meeting areas | Kg | 848,085.00 | 895597 | 1810351 | 978739 | 3121625.84 | **7,654,397.34** |
| | House to house solid waste collection & transport | Kg | 148,892.66 | 273026 | 871584 | 0 | 864184.824 | **2,157,687.48** |
| | River side cleaning (Lake cleaning) | Kg | - | 287086 | 0 | 377532 | 327908 | **992,526.02** |
| | Illegal dumping site cleaning | Kg | 371,383.50 | 418530 | 233091 | 422102 | 1240039.74 | **2,685,145.87** |
| | open drainage cleaning | ML | 259,387.16 | 265070 | 391513 | 665229 | 849748.824 | **2,430,947.80** |
| | Closed drainage cleaning | ML | 28,230.30 | 104352 | 82737 | 124148 | 0 | **339,466.85** |
| | **Total** | | | | | | | 25,097,144.56 |
| 2 | **Urban Beautification & greenery** | | | | | | | |
| | Site preparation | Ha | 0 | 9 | 5.5 | 20.52 | 33 | **67.62** |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | Pitting (digging pits) | Ha | 37542 | 1269 | 208528 | 53148 | 398,660 | **699,147.00** |
| | Watering | No | 50 | 31 | 14.6 | 112.4 | 148 | **356.30** |
| | Weeding | No | 50 | 54 | 8.7 | 99.9 | 149 | **361.60** |
| | Shrub planting | No | 93440 | 0 | 15000 | 40120 | 250,360 | **398,920.00** |
| | Flower bed establishment | No | 0 | 0 | 0 | 57250 | - | **57,250.00** |
| | Forest tree planting | No | 200 | 659 | 237292 | 18717 | 168,510 | **425,378.00** |
| | Fruit tree planting | No | 32000 | 358 | 75313 | 22592 | 1,792 | **132,055.00** |
| | Seedling production | Ha | 18200 | 0 | 0 | 127902 | - | **146,102.00** |
| | Lawn grass establishment | LM | 0 | 0 | 0 | 3 | - | **3.00** |
| | Manuring of planting pits | Ha | 0 | 0 | 0 | 862690 | - | **862,690.00** |
| | Water line installation | No | 0 | 0 | 0 | 119153 | - | **119,153.00** |
| | Leveling | | 0 | 0 | 0 | 7.01 | 0 | **7.01** |
| | Tree pruning | | 10236 | 0 | 0 | 13090 | 0 | **23,326.00** |
| **3** | **Urban Integrated Watershed Development Activities** | | | | | | | |
| A | **Physical Soil and Water conservation Activities** | | | | | | | **-** |
| | Hilside Terracing | Km | 1 | 0 | 0 | 0 | 0 | **1.00** |
| | Level &graded soil bund construction | Km | 3 | 0 | 0 | 0 | 66.9 | **69.90** |
| | Gully Reshaping (Fill &Leveling) | $M^3$ | 0 | 0 | 0 | 0 | 673 | **673.00** |


| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | Loose stone check dam construction | M³ | 0 | 0 | 0 | 4337 | 119 | **4,456.00** |
| | Sand bag check dam construction | M³ | 0 | 0 | 0 | 0 | 22 | **22.00** |
| | Brush wood check dam construction | LM | 0 | 0 | 0 | 0 | 310 | **310.00** |
| | Gabion construction | M³ | 45 | 0 | 0 | 0 | 0 | **45.00** |
| | stone collection | M³ | 59 | 0 | 0 | 2170 | 281 | **2,510.00** |
| | stone transportation | M³ | 59 | 0 | 0 | 2170 | 281 | **2,510.00** |
| | Micro Tranches | NO | 0 | 8 | 0 | 0 | 0 | **8.00** |
| B | **Biological soil and water conservation Activities** | | | | | | | **-** |
| | Seedling production | No | 10000 | 0 | 0 | 0 | 44630 | **54,630.00** |
| | Planting on bunds | km | 0 | 0 | 0 | 0 | 6 | **6.00** |
| | Vegetative fencing & stabilization | Km | 3 | 0 | 0 | 0 | 2.8 | **5.80** |
| | Bund stabilization (grass & Legumes) | km | 0 | 0 | 0 | 0 | 22 | **22.00** |
| | Seeddling planting | No | 5543 | 0 | 0 | 0 | 0 | **5,543.00** |
| 4 | **Creating Favourable Condition For Urban Agriculture** | | | | | | | |
| | Illegal dumping site cleaning | Ha | 3.5 | 28 | 0 | 22.16 | 16 | **69.16** |
| | River side cleaning | Ha | 0 | 3.5 | 0 | 26.92 | - | **30.42** |
| | River side green development | Ha | 0 | 0 | 0 | 3.17 | - | **3.17** |
| | Gully cut&fill/reshaping/leveling | Ha | 0 | 0 | 1 | 0 | 2 | **2.50** |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 5 | **Small Infrastructure** | | | | | | | |
| | Latrine construction | No | 1 | 0 | 0.65 | 0 | 1 | **2.65** |
| | Sand transportation | M3 | 0 | 0 | 210 | 6 | 0 | **216.00** |
| | Stone collection and transportation | M3 | 14 | 0 | 224 | 141.17 | 0 | **379.17** |
| | Road maintenance | Km | 0 | 2.8 | 0 | 0 | 1 | **3.80** |
| | Construction material loading unloading | Qt | 0 | 0 | 0 | 677.3 | 0 | **677.30** |
| | Rehabilitation/Construction of class room | Roo m | 0 | 0 | 0 | 0 | 4 | **4.00** |
| | Water Line construction | M | 0 | 0 | 9 | 0 | 0 | **9.00** |
| | Constructing Child care centers | No | 2 | 0 | 0 | 0 | 0 | **2.00** |
| | Tent | No | 0 | 0 | 0 | 6 | 0 | **6.00** |


### 4.4. የአካባቢ ልማት ሥራዎች ጠቀሜታ

የአካባቢ ልማት ሥራዎች  የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና ማስወገድ፣ አረንጓዴ ልማት፣ የተፋሰስ ልማት፣ ከተማ ግብርና እና ተያያዥ የአነስተኛ መሠረተ ልማት ሥራዎች በኢኮኖሚያዊ፣ በማህበራዊእና አካባቢያዊ  ጥቅሞች እንዳላቸው ጥናቶች አረጋግጠዋል፡፡


በዚህ ፕሮጀክት የተሰሩ የአካባቢ ልማት ሥራዎች  ለህብረተሰቡና ለአካባቢው ከፍተኛ ውጤትና ጠቀሜታ እያመጡ እንደሆነ በዚህም ጥናት የተሳተፉ የሚስማሙ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል፡፡




በፕሮጀክቱ ተግባራዊ እየሆነ ያለው የአነስተኛ መሠረተ ልማት ሥራ በፕሮጀክቱ ከተሞቫ አገልግሎት እየሰጠ መሆኑን ከህብረተሰቡ የተወከሉ የጥናቱ ተሳታፊዎች ይስማማሉ፡፡




በቀታይም የተጠናቀቁ የአነስተኛ መሠረተ ልማት ሥራዎች በዘላቂነት 72 % ተጣቃሚዎች ባለቤት ሆነው ቢጠቀሙ እንደሚፈልጉ  52 % ህብረሰቡ ደግሞ ህብረሰቡ እንድያዘ እንሚመረጥ በዚህ ጥናት ተላቷል፡፡





## 4.5 የአካባቢ ልማት ሥራዎች ፍይዳዎች

### I. ማህበራዊ ፋይዳዎች

#### 4.5.1. በህብረተሰቡ እና የተጠቃሚዎች ግንዛቤና ክህሎት እና የሥራ ባህል ፋይዳ

በህብረተሰቡና በተጠቃሚው ያለው ስለፕሮጀክቱ የአካባቢ ልማት ሥራ የግንዛቤ ደረጃ ከፍተናና በጣም ከፍተኛ 68.9 % ነው፡፡




ቀደም ሲል ፕሮጀክቱ ወደ ከተማው ከመምጣቱ በፊትና ተጠቃሚዎችም በፕሮጀክቱ ከመታቀፋቸው በፊት ተጠቃሚዎችና ህብረተሰቡ በአካባቢ ልማት ሥራዎች ላይ ያለቸው የግንዛቤ በመለወጥ አሁን የሚከተለውን ለውጥ አምጠቶላቸዋል ብለው እንደሚያምኑ የቴክኒክ ኮሚቴ የሆኑት ከህብረተሰቡ የተወከሉት የጥናቱ ተሳታፊዎች በውይት ወቅት የሚከተለውን አረጋግጠዋል

- በደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አስተሳሰብና የአመለካከት ለውጥ ከማምጣቱም በላይ በደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ላይ በቂ ዕውቀትና የክህሎት መሻሻል አምጥቷል
- ቆሻሻ የትም መጣል የለበትም የሚል አረዳድ መምጣቱ

- ሥራ ክቡር እንደሆነ በመገንዘብና የሥራ ተነሳሽነት ለውጥ መኖሩ
- ሥራው የገቢ ለውጥ እንዲኖር የሚያስችል መሆኑ አረዳድ መምጣቱ
- የህብረተሰቡን ጤና ለመጠበቅ ጥቅም እየሰጠ መሆኑን አረዳድ መኖሩ
- በሁሉም የከተማ አካባቢዎች የከተማ ውስጥ ግብርና ጥቅምን በማጉላት በስፋት እንዲስፋፋ አስተዋጾ አበርክቷል፣ አስተምሯል
- የባንክ ሲስተም እና ባንክ ምን እንደሆነ የማያውቁትን የባንክ ተጠቃሚ አድርጓል፣ ቁጠባን አሳድጓል
- የሥራ ፍላጎት በሌላቸው የተጠቃሚና የህብረተሰቡ አባላት ላይ ሥራን የማክበርና የሥራ ፍላጎትንና ባህልን አሳድጓል እንደዚሁም የሥራ ፉክክርን አምጥቷል
- በግልና በጋራ የሥራ ተነሳሽነት አምጥቷል፣ ሥራን በመሥራት ራስን፣ አካባቢን፣ ከተማን መለወጥ እንደሚቻል ግንዛቤ ተይዟል
- በሁሉም ባለድርሻ አካላት ማለትም በተጠቃሚው፣ በኮሚቴ፣ በተቋማት ላይ በሥራ ቁርጠኛ እንዲሆኑ አስችሏል። ለምሳሌ ተጠቃሚዎች እና ህብረተሰቡ ቆሻሻን ማጽዳት ነውር እንዳልሆነ ይልቁንም ለአንድ ከተማ አስፈላጊ ተግባር እንደሆነ ግንዛቤ ተይዞዋል
- ሳይንሳዊ የሆነ የንግድና የሥራ ዕውቀትን ባህልን አሳድጓል
- በደረቅ ቆሻሻ አወጋገድ ላይ ክህሎትን አሳድጓል፣ ለምሳሌ ቆሻሻ ማቃጠል ተገቢ እንዳልሆነ፣ ቆሻሻን ለይቶ መሰብሰብ … በመሳሰሉት የተሸለ ግንዛቤ መጥቷል
- የከተሞች የአረንጓዴ ቦታዎችን ማልማትና መጠበቅ ላይ ክህሎትና ግንዛቤ መጥቷል
- ቆሻሻን ለማጽዳት ያለው ጥላቻና አመለካከት ተለውጧል፤ የቆሸሻ አካባቢ ለጤና ጠንቅ መሆኑን በመሆኑ ቆሻሻን ማስወገድ አስፈላጊ መሆኑን ግንዛቤው መጥቷል።
- በከተሞች በመጣው ግንዛቤና የትብብር መንፈስ አሁን በየቦታው ቆሻሻ የሚጥል የለም
- ቀደም ሲል ቆሻሻ ማንሳት ያለባቸው የሚከፈላቸው የሴፈቲኔት ተጠቃሚዎች ብቻ አርጎ የማዬት ነገር ነበር አሁን ተቀይሮ ሁሉም በትብብር የሰራል
- የአካባቢ ልማት ሥራዎችን ባለቤት አድርጎ የመውሰድ ግንዛቤ መጥቷል

### 4.5.2. ለእርስ በርስ ማህበራዊ ትስስር


- የተጠቃሚዎች የእርስ በርስ ትውውቅ፣ መረዳዳትና መጠያየቅ አምጥቷል
- ህብረተሰቡና ተቋማት እርስ በርስ እንዲተዋወቁና እንዲረዳዱ እና አብረው እንዲሰሩ ማቀራረብ መቻሉ
- በህብረተሰቡ ዘንድ በጋራ መሥራትን ባህል አሳድጓል ለምሳሌ አብሮ በመፅዳት
- በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የነበሩ ተጠቃሚዎች የሚሰማቸውን የዝቅተኝነት ስሜት በገቢ ለውጥና በመጣው የኑሮ ለውጥ ምክንያት ሥነልቦናቸው ታክሞ በማህበረሰቡ ውስጥ በማህበራዊ ኑሮ መቀላቀል አስችሏል። በህብረተሰቡም ተቀባይነታቸው ጨምሯል።
- ሥራዉ የሚሰራው በብዙ ባለድርሻ አካላት ትብብር በመሆኑ ቅንጅታዊ አሰራርን አሳድጓል፣
- ተቋማት ተቀራርበው በውይት ሃሳብ እንዲለዋወጡ፣ እንዲማማሩ ዕድል ከፍቷል፣ የቡድን ሥራን አሳድጓል
- ባጠቃላይ በተጠቃሚዎች ስሜት ላይ የኑሮ ተስፋ የሰጣቸውና ደስተኛ ሆነው መኖር እንዲጀምሩ አስችሏቸዋል
- በከተሞች እጅግ የቆሸሹና ድብቅ ቦታዎች ወንጀል የሚሰራባቸው፣ የሺሻ ማጨሻ የነበሩ ቦታዎች ፀድተው ህብረተሰቡ ከላይ ከተጠቀሱት ችግሮች በማላቀቅ የመናፈሻ ወይም የግብርና ቦታ መሆናቸው

- ህብረተሰቡ በአረንጓዴ ልማትና እንክብካቤ አብሮ በመሥራት በመጠበቅ በተግባር አብሮ እየሰራ መምጣቱ ከፕሮጀክቱ ጋር ይያዛል
- በአሁን ሰዓት ሁሉም የፕሮጀክቱ ቤተሰብና ተጠቃሚ መሆን ይፈልጋል
- በዚህ ፕሮጀክት ምክንያት በየከተማው ተቋማዊ መደጋገፍ ዳብሯል
- በህብረተሰቡ መተጋገዝንና መተባበርን ስሜት አዳብሯል
- ህብረተሰቡ የማይሳተፍበት ልማት ዘላቂ አይሆንም በሚል መርህ የለሙ የአረንጓዴ ቦታዎችን በመጠበቅ፣ ትናንሽ አትሮችን በማጠር እደገፈ ይገኛል
- በህገወጥ መንገድ ቆሻሻ ሲጣል ወዲያው ለሚመለከተው አካል በመጠቆም እርምት እንዲያገኝ ይተባበራል

- ዕድርና ዕቁብ ውስጥ ለመሳተፍ የማይችሉና የሥነ ልቦና ጫና የነበራቸው በነጻነት መሳተፍ ችለዋል

### 4.5.3. ማህበራዊ ድጋፍ ትስስር

**ከየፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎ የማህበራዊ ትስስር ተጠቃሚ መሆን እንደቻሉ ይህ ጥናት ያሳያል**




**ሀ. በግለሰቦች በተቋማት እና በህብረተሰቡ ማህበራዊ ትስስር መዳበር**

- በማህበራዊ ትስስር ተጠቃሚወች እእየደገፉ ነው ለምሳሌ ግለሰቦች የትምህርት ግብዓትና የመሳሰሉትን በማቅረብ፤ ተቋማትም ዱቄትና ሳሙና እደገፈ ገኛል
- ህብረተሰቡ በመተባበር ለተጠቃሚዎች የመኖሪያ ቤት ተገንብቷል
- ተጠቃሚዎች እርስ በርስ በመደጋገፍ ጭምር የመኖሪያ ቤት ጥገና አድርጓል/ ተገንብቷል
- በጎልማሳ ትምህርት የትምህርት አቅርቦት አገኙ መሆናቸው
- በትምህርት፣ በገብዓት እና በአሰራር ተቋማዊ ቅንጅት ማጎልበት




**ለ. ተጠቃሚዎች ተጨማሪ ድጋፍ ማግኘት በመቻላቸው ቤተሰቦቻቸውን የማኖር አቅም አግኝተዋል**

- የት/ርት ግብዓት ደብተርና እስኪሪብቶ፣ የትምህርት አቅርቦት፣
- የጤና ኢንሹራንስ ክፍያ ተሸፍኖልኛል
- ልጅ በነፃ እንዲማር  የትምህርት ክፍያ ተሸፍኖልኛል
- በተጨማሪ ምግብ አቅርቦት፣ የሳሙና ድጋፍ
- የመኖሪያ ቤት እድሳት፣ አዲስ የመኖሪ ቤት ስጦታ




ቢሾፍቱ ተማሪዎች በፕሮጀክቱ በተገነባ ት/ ቤት በክፍል ውስጥ



### 4.5.4. የህብረተሰቡ ድጋፍ

ህብረተሰቡ የፕሮጀክቱን አስፈላጊነት በማመን በሚከተሉት መንገዶች በመደገፍ ተሳታፊ ሆኗል፡፡

- የአረንጓዴ ቦታዎችን አጥር በማጠርና በመጠበቅ
- ዛፎችን በግቢአቸውና ከግቢ ውጭ በመትከል፣ በመንከብከብ
- ከግቢ ውጪ ያሉ ቦታዎችን ለከተማ ግብርና በመፍቀድ
- የቀረቡ ምርቶችን መጠቀም
- የአነስተኛ መሠረተ ልማት የግንባታ ቁሳቁሶችን በመጠበቅ
- ግንባታ ድጋፍ በማድረግ
- የፕሮጀክቱ ባለቤትና ተጠቃሚ ነኝ ቦሎ ያስባል
- አካባቢያቸውን አብሮ በማጽዳት

ያለውን የውሃ አቅርቦት ችግር በመረዳት ህብረተሰቡ በየበሩ ያለውን ውሃ በማጠጣት አብሮ እየሠራ ይገኛል

- ችግኝ ገዝቶ የችግን ድጋፍ እደረገ ይገኛል
- የግንባታ ሥራ ሲሰራ የግንባታ ቁሳቁስ ለምሳሌ ሲሚንቶ በማቅረብ ይተባበራል፤ ውሃ የሚያጠጣው ህዝብ ነው፣ የሙ ድጋፍም በማድረግ የተባበራል
- የመንገድ ሥራዎች ላይ ህብረተሰቡ አብሮ በመሥራት ይተባበራል
- በግቢያቸው ትርፍ መሬትን በማቅረብ እና ዘር በመግዛት ህብረተሰቡ እየደገፈ ነው

## II. ኢኮኖሚያዊ ፋዳዎች

### 4.5.5. የምግብ አቅርቦት፣ የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥና የጤና ፋይዳ

የከተማ የአካባቢ ልማት ሥራ ለነዋሪው በግል እና በቡድን በቤተሰብ ከሚሰጠው ጥቅም ባሻገር ለሀገራዊ የኢኮኖሚ እድገትም አስተዋጽኦ አለው ተብሎ ይታመናል፡፡ ለዚሁም ምክንያቱ የከተማ ግብርና እና የአትክልትና ፍራፍሬ ልማት ለከተማው ህዝብ መሠረታዊ የምግብ ፍላጎትን በተለይም በጓሮ አተክልት በማርካት የከተሞችን የኢኮኖሚ አቅም በማጠናከር የምግብ አቅርቦት፣ የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥና የጤና ፋይዳ እንዳለው ጥናቶች አመልክተዋል፡፡

የከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮጀክት ወደ በየከተማው ከመጣ በኋላ የአካባቢ ልማት ሥራዎች ተግባራዊ በመሆናቸው  አሁን የምግብ ዋስትናን በማረጋገጥና ጤናን በማስጠበቅ ፕሮጀክቱ የሚከተለውን ውጤት አምጠቶላቸዋል ብለው እንደሚያምኑ ለዚህ ጥናት የተለዩ የቴክኒክ ኮሚቴ የሆኑትና ከህብረተሰቡ  የተወከሉት የጥናቱ ተሳታፊዎች በውይት ወቅት አረጋግጠዋል፡፡

### ሀ. ፍትሃዊ የመሬት አጠቃቀም እንዲኖር

- በየቤቱ ያሉ ባዶ ቦታዎች በጓሮ አታክልት እዲሸፈኑ አድርል
- በከተማ ውስት ያሉ በጊዜያዊነት ባዶ ሆነው ያሉ ቦታዎች በወጣቱና በማህበረሰቡ ለግብርና ሥራ እየተጠየቁ እና ጥቅም ላይ መዋሉ

### ለ.የምግብ አቅርቦትና የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥና የጤና ፋይዳ

- የግብርና የፍጆታ ምርቶች በርካሽ ገበያ እንዲቀርብ አስችሏል
- በግለሰቦችና ተቋማት ባዶ የነበሩ ቦታዎች ወደ ልማት መዞራቸው በከተማ ግብርና የጓሮ አትክልትና ሌሎች የግብርና ውቴቶችን አቅርቦት በማሳደግ የህብረተሰቡን ፍላጎት ለማርካት ሞክሯል
- በሁሉም የከተማ አካባቢዎች የከተማ ውስጥ ግብርና በስፋት ተግባራዊ ማድረግ በመጀመሩ በዚህ ሰፊ የተለያዩ የምግብ ውጤቶች በርካሽ ማግኘት በመቻሉ ረሀብን በማስወገድ የምግብ አወሳሰድን በማሻሻል የህብረተሰቡ ጤና ላይ ውጤት እያመጣ ይገኛል፡፡




### 4.5.6. የገቢ ምንጭና የሥራ ዕድልን በመፍጠር ያለው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ

በፕሮጀክቱ የሚተገበሩ በአካባቢ ልማት ሥራዎች በፕሮጀክቱ ለታቀፉ ተጠቃሚዎች የገቢ ምንጭና የሥራ ዕድልን በመፍጠር የሚከተለውን ውጤት አምጠቶላቸዋል ብለው እንደሚያምኑ ሁሉም የትናቱ ተሳታፊዎች በውይት ወቅት አረጋግጠዋል

**ሀ. የሥራ ዕድል ፈጠራና የገቢ ምንጭ፣**

- የተቃሚዎችን ገቢ በማሳደግ ኑሮአቸውን አሻሽሏል
- ለተጠቃሚዎች በሚደረግ ክፍያ ገበያን በየወሩ ያነቃቃል
- የሴፍቲኔት ተጠቃሚ መሆን በመጀመራችን በተለያዩ ሥራዎችና የንግድ ዘርፍ በመጀመር ተጠቃሚ ሆነናል፡፡ ለምሳሌ ባልትና፣ የአታክልት ችርቻሮ…
- በተጠቃሚዎች ዘንድ የቁጠባ ባህልን ማስደጉ እና ለተጨማሪ ገቢ እንዲሰሩ አቅም የፈጠረላቸው መሆኑ
- የገቢ ምንጭ በማሳደግ ተጨማሪ ገቢ ማግኘት አስችሏቸዋል
- በተሰማሩበት መስክ መሥራታቸው የንግድና የሥራ ክህሎት እያገኙና እንዲያሳድጉ የጠቀማቸው መሆኑ
- የባንክ ሲስተም እና ባንክ ምን እንደሆነ ማወቅ በመቻላቸው የባንክ ተጠቃሚ በመሆናቸው በነበራቸው ቁጠባ እና ግራነት ክፍያ ተጨማሪ ሥራ ላ ተሰማርተው ገቢያቸውና የመስራት አቅማቸውን አሳድጓል

- ገቢያቸው እንዲጨምር የሥራ ላይ ገኙት የኢኮኖሚ ትምህርት የመስራት ፍላጎታቸው ጨምሯል፣ የሥራ ባህል ተለውጧል፣ የሥራ ሥነ ልቦና እንዲኖራቸው ያስቻለ በመሆኑ ሰርቶ በመኖር ኑሮአቸው ተሻሽሏል፡፡
- የከተማ ግብርና ባህልን አሳድጎ፤ ህብረተሰቡ በጓሮ አትክልት በከብት እርባታ፣ በዶሮ እርባታ እንዲሰማራ እያደረገ  የገቢ ምንጭ ሆኗል
- ምንም መሥራት የማይችሉና የመሥራት አቅም የሌላቸው ተጠቃሚዎች ካፒታል እንዲኖራቸው በመድረግ ወደ ሥራ እንዲገቡ አስችሏል

# III. አካባቢያዊ ፋይዳዎች

## 4.5.7. ለዘላቂ የከተሞች ዕድገት ያለው ፋይዳ

### ሀ.የከተሞችን አካባቢ ልማትና የገጽታ ለውጥ


- በከተማ ውስጥ ቀደም ሲል የነበሩትን በመንከባከብን እና አዲስ የሚተከሉ የአረንጓዴ ተክሎች የከተማውን ውበት በመጠበቅ አስተዋጾ አላቸው
- ሰዋራ አካባቢዎች ፀድተው ህገወጥ የቆሻሻ መጣይ ሥፍራዎች እንዳይኖሩና ቀደም ሲል የነበሩት ፀድተው የመናፈሻና የግብርና ቦታ እንዲሆኑ አስችሏል፡፡
- በአንዳንድ አካባቢዎች የነበረው ሽታ ተወግዶ ንጹህ አየር መተንፈስ ችለዋል
- ከዚህ በፊት ለማየት የሚያስጠሉ ቦታዎች ወብ በመሆናቸው የእይታና የሥነልቦና እርካታ አምጥቷል፡፡
- በግልና በጋራ ሥራን በመሥራት ራስን፣ አካባቢን፣ ከተማን በአካካባቢ ጥበቃና በማህበረሰብ አቀፍ ግንዛቤና ጤና እንዲሁም ኢኮኖሚ የእድገት ለውጥ አምጥቷል፡፡




### ለ. ለተፈጥሮ ሐብት ጥበቃና ለአደጋ መከላከል ያለው ጥቅም

- በጋራ በቀንጅታዊ አሰራር የደን መጨፍጨፍ እንዳይኖር በመከላከል ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል፡፡

- የከተማ የፍሳሽ መሥመሮች ሞልተው የከተማ ጎርፍ እንዳፈጠርና ጎርፍን ለመከላከል ቱቦ ጠረጋ እየተሰራ በመሆኑ የሚፈጠሩ አደጋዎች በመቀነስ ፋይዳ አለው
- በከተሞች እጅግ የቆሸሹና ድብቅ ቦታዎች ወንጀል የሚሰራባቸው፣ የሺሻ ማጨሻ የነበሩ ቦታዎች ፀድተው ህብረተሰቡ ከላይ ከተጠቀሱት ችግሮች በማላቀቅ የመናፈሻ ወይም የግብርና ቦታ መሆናቸው
- ይህ ፕሮጀክት ባይኖር ቆሻሻው ከከተማው አቅም በላይ ሆኖ ብክለት ይጨምር ነበር




**ሐ. ለከተሞች ቆሻሻ አያያዝ ያለው ጥቅም**

- ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ተጥለው በቆሻሻ የተሞሉና አካባቢዎችን ንፁኅ በማድረግ የገፅታ ለውጥ እንዲኖር በማስቻል
- የማዘጋጃ ቤትና የህብረተሰቡን የወጪ ሸክም ቀንሷል
- በፕሮጀክቱ ምክንያት ቀደም ሲል በግቢ ውስጥ ብቻ ተወስኖ የነበረው የፅዳት ደረጃ ከግቢ ውጭ ያለውን ጨምሮ ወደ ማጽዳት ተሸጋግሯል
- ህብረተሰቡ ከተጠቃሚዎች ጋር በመሆን አካባቢያቸውንና ከተማውን ማጽዳት ጀምሯል
- ከተማው ፅዱና ውብ እንዲሆን አስችሏል፡፡ የፕሮጀክቱ የአካባቢ ልማት ሥራ የከተማው አስተዳደር የፅዳትና የአረንጓዴ ልማት ወጪን ቀንሷል፡፡
-




### መ. ለውጤታማና ሳይንሳዊ የመሬት አጠቃቀምና የከተማ ፕላን አፈጻጸም

- በከተሞች ፕላን ለአረንጓዴ ልማት  የተተው ቦታዎችን ከተሞች በተገቢው መንገድ ለአረንጓዴ ልማት ማዋል እንዲችሉ አቅም በመሆን የመንገድ ዳርቻዎችን አካፋዮችን፣ ፓርኮችን፣ የወንዝና የሐይቅ ዳርቻዎችን የመሳሰሉትን በማልማት የፕላን ጥሰት ለመከላከል አስችሏል






## 4.6. መሻሻል እና መሟላት ያለባቸው ጉዳዮች

- በደረቅ ቆሻሻ ላይ የህብረተሰቡ አረዳድ በዕኩል ደረጃ ላይ አለመሆኑ አልፎ አልፎ ህጋዊ ያልሆኑ የቆሻሻን በየቦታው መድፋትና መልሶ ማቆሸሽ ነገር በጥቂቶች መኖሩ
- በጥቂቶች የቁርጠኝነት ማነስ
- በተወሰነ ደረጃ ለተጠናቀቁ ት/ቤቶች የሌሎች ግብዓቶች ጠባቂ መሆን ለምሳሌ ጠረጴዛ፣ ወንበር…
- የቆሻሻ መኪና አለመኖር
- የህጻናት ማቆያ ድንኳን ምቹ አለመሆን
- የተደራጀ ሃይል ስለሆነ ለፖሊቲካ ፍጆታ ለመጠቀም ጫና መኖሩ
- IGA ከከተማ ግብርና ላይ ብቻ መቆራኘቱ
- የሥራ ቦታ አቅርቦት ችግር
- የለሙ ቦታዎችን ባለቤት መቀየር
- የባለሞው ዕለታዊ ውሎ አበል ማነስ 125.00 ብር
- ተጠቃሚዎች ይከፈላቸዋልና ያፅዱ የሚል አመለካከት መኖር
- የተጠቃሚዎች ዕለታዊ ክፍያና የሥራ ሰዓት ከኑሮ ውድነት ጋር ተዳምሮ አለመጣጣም

- ጎባና ሮቤ አንድ ከተማ ቢሆኑም ተጠቃሚዎች የተመለመሉት ከሮቤ ብቻ መሆኑና ኮታው በጣም አነስተኛና ከተማው ጥያቄ አንጻር የማይመጣጠን መሆኑ 5998
- ለጠቃሚዎች በትርፍ ጊዜ የመሥሪያ ቦታ አቅርቦት
- በኪራይ ቤት  የሚኖሩ ተጨማሪ ሥራዎችን ለምሳሌ ንግድ፣ ከብት፣ ዶሮ ማርባት እፈለጉ አለመቻላቸው
- የጎባ ተማ የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ አመሆኑ፣ በአቅራቢ ሆኖ ቆሸሸ

መሆኑ

- የአመራሩ መለዋወጥ ፈጣን በመሆኑ ስለሥራው የሚቀርበው ተከታታይ ሥልጠና በዚው ልክ አለመሆኑ
- የአመራሩ ቁርጠኛነት ውስንነት
- በተጠቃሚዎች ዘንድ የራስ መጠበቂ አልባሳት ለመጠቀም ያለው ፍላጎት በተወሰኑት ላይ ዝቅተና መሆን
- በፌዴራል ኖ ኦብጀክሽን መዘግት ምክንት የፕሮጀክቱ ሥራ መጓተት
- የፕሮጀክቱ ዋናዋና ሥራዎች በፎካል ሰዎች እየተመሩ መሆኑና የሥራ መደራረብ መኖሩ
- የዲሲይን ጥራት መክንያትና በሌሎችም ምክንያቶች ፕሮጀክቶች ሲዘገዩ በጀት ላይ ተመላሽ የመሆን እና ያለው የዋጋ ንረት ከፍተኛ ስለሚሆን በቀጣይ ትግበራ ላይ ተፅዕኖ ማሳደር
- አልፎ አልፎ ቆሻሻን አውቆ በየቦታው መጣል፣ አንዳንድ በታዎችን ለህገወጥ ቆሻሻ ማጠራቀሚያነት መጠቀም
- በማዘጋጃ ቤት በኩል ከጊዚዊ ቆሻሻ መሰብሰቢያ ቦታ በፍጥነት አለማንስትና ማቆየት በዚህም ከአካባቢው ማህበረሰብ ጋር ጭቅጭቅ መኖሩ
- በሥራ ሰዓት ከሁለት ሰዓት በኂላ በየመንገዱ ቆሻሻ ሲጠረግ ከመንገደኛ ጋር ጭቅጭቅ መኖሩና በህበረተሰቡ ጤና ላይ ተፅዕኖ ማሳደሩ
- የተጠቃሚዎችን ሞራል ሊጎዳ የሚችል ንግግርና ስድብ መኖሩ
- የውሃ አቅርቦት ችግር
- የኑሮ ውድነትን ያላገናዘበ እለታዊ ክፍያ መኖሩ በተጠቀሚዎች ላይ በስራ ቀናት/ሰዓት ምክንያት ጫና ማሳደሩ
- ከከተማው ዕድገት አንጻር የተሰተው ኮታ በጣም አነስተኛ በመሆኑ የመሥራት ዕድል የተገደበ መሆኑ
- የፕሮጀክቱ የቆታ ጊዜ 3 ዓመት ብቻ መሆኑና ዕለታዊ ክፍያ 150 ብር በመሆኑ በኑሮ ውድነት ምክንያት በሁሉም ተጠቃሚ ሙሉ በሙሉ የኑሮ ለውጥ ለማምጣት አስቸጋሪ መሆኑ
- PMT ዋናው መለኪያ የቤተሰብ ቁጥር በመሆኑ በጣም በችግር ላይ ያሉ የአካል ጉዳተኞች መረዳት የሚገባቸው ቤተሰቦች ተጠቃሚ መሆን ልቻሉበት ሁኔታ መኖር
- ተጠባባቂዎች ዝርዝር ላይ የተካተተትን በተሳሳተ መንገድ በአጭር ጊዜ ውስጥ ዕድሉን አገኛለሁ በሚል ተስፋ ወደ አስተባባሪ ፅ/ቤት በተደጋጋሚ የመመላለስ ችግር መኖሩ
- በደረቅ ቆሻሻ አያያዝ ላይ ቀሪ ሥራዎች መኖራቸው
- የግብአት አቅርቦት በተለይ ቆሻሻ ማንሻ
- ዕለታዊ/ ወርሃዊ ክፍያ ከወቅቱ የኑሮ ውድነት አንጻር ዝቅጸና መኖኑ
- ሥራው በጣም አድካሚና ዕለታዊ ክትትል የሚፈልግ ሆኖ ሳለ ለፈፃሚዎች ወርሃዊ ደሞዝ ተመጣጣኝ አለመሆኑ
- የአመራሩ የክትትልና ድጋፍ በራቀ ጊዜ በየ ሶስት ወር መሆኑ የፌዴራል ክትትልና ድጋፍ በዚያው ልክ ተከታታይ አለመሆን

## ክፍል አምስት

# 5. ማጠቃለያና ምክረሃሳብ

## 5.1.ማጠቃለያ

የከተሞች የምግብ ዋስትና ፕሮጀክት በከተሞች ከድህነት ወለል በታች የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን ገቢያቸውን በማሻሻል በከተሞች የተንሰራፋውን ድህነት ለመቀነስ ዓላማ ያደረገው ፕሮጀክት ተጠቃሚዎችን በአካባቢ ልማት ተሳታፊ በማድረግ ባጠቃላይ የሚከተሉት ስኬት ማስመዝገብ ችሏል፡፡

- ምንም የሌላቸው ተጠቃሚዎች የምግብ ዋስትናቸው ተሻሽሏል ፣ ቤተሰቦቻቸውን መመገብና ማስተማር ችለዋል
- በተጠቃሚዎች የሥራ ካፒታልን በማሳደግ ከፌስታል መጠን ወደ ኩይንታል ንግዳቸውን ማሳደግ አስችሏል
- የከተማውን ንፅኅና በማስጠበቅ የገፅታ ለውጥ አምትቷል
  የአየርና የውሃ ብክለትን በመቀነስ በፅዱ ከተማ የሚኖር ማኅበረሰብ ሆኖ ጤናውና ሥነ ልቦናው ተለውጦ ደስተኛ ማህበረሰብ እየፈጠረ ይገኛል፡፡
- ማህበራዊ ትስስርን አዳብሯል፣ ዕድር፣ መተጋገዝን አምጥቷል
- በከተማ ደረጃ ባሉ ተቋማት ቅንጅታዊ አሠራርን አዳብሯል
- በዕድገት መለኪያ ሲገመገም ለከተማው ዕድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እበረከተ ያለ ፕሮጀክት ነው ተብሎ ይታመናል
- ባጠቃላይ ፕሮጀክቱ ዋና ዓላም ሆኑት በዝቅተና የኑሮ ደረጃ ላይ ሆነው ኖሮ ከብዷቸው ለነበሩ የድሃውን ማህበረሰብ የምግባ ዋስትና በማረጋገጥ ሰብአዊ ድጋፍ ሥራና የአካባቢ ጥበቃ ሥራ ም በፕሮጀክቱ አፈጻጸም ሲታይ ዓላማው የተሳካ ነው ለማለት የሚያስችልል በጥናቱ ተመላክቷል፡፡

## 5.2. ምክረሃሳብ

- በከተማ ደረጃ ያለው መዋቅር ሥራው አድካሚ በመሆኑ የሰው ሃይል፣ የደሞዝ ስኬል ቢከለስና ግብዓት አቅርቦቱ ክትትል ተደርጎ ቢሻሻል
- በአመራሩ መለዋወጥ ምክንያት ሥራው እንዳይበደል ተከታታይ ሥልጠና ቢሰጠው
- የአመራሩ ቁርጠኛነት
- ያለው ከፍተኛ የዋጋ ንረት ሚቋቋም የሚችል ካፒታል በጀት ቀመር ቢመጣና ቢሻሻል
- በቀበሌና በቀጠና ደረጃ በአዲስ የመኖሪያ ቤትና የሥራ ቦታ ግንባታ ካፒታል ላላቸው ተጠቃሚዎች የአቅርቦት ዕድሉ ቢሰጣቸው
- በፕሮጀክቱ ኮታ አሰጣጥ መለኪያዎች የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ ቢያገናዝብ፣ የቆዩ መረጃዎች ጥቅም ላይ ባይውል
- የጎዳና የመንገድ ጽዳት ከሁለት ሰዓት በፊት እንዲጠናቀቅ ቢደረግ
- የህብረተሰቡን ግንዛቤ ለማሳደግና ለፕሮጀክቱ ተባባሪና ደጋፊ እንዲሆን የተለያዩ የመገናኛ ዜዴዎች ጥቅም ላይ ቢውሉ
- የአመራሩ የክትትልና ድጋፍ በራቀ ጊዜ በየወሩ ቢሆን እና የፌዴራል ክትትልና ድጋፍ በዚያው ልክ ቢያንስ በየሩብ ዓመቱ ተከታታይ ቢሆን
- የአረንጓዴ ልማት ለውበት ተጠናክሮ ቢቀጥል፣ የመንገድ ዳርቻ ሥራዎች በሥፋት ቢሰሩ፣ የሠፈር ውስጥ ባዶ እና መዝናኛ ቦታዎች ትኩረት ቢሰጣቸው
- በከተማ ለሰርግ አገልግሎት የሚውል መዝናኛ ቦታ ልማት ቢሰራበት

- የህብረተሰብ ንቅናቄ ግንዛቤ ቢፈጠር
- የተጠቃሚዎች ኮታው ቢሰፋ
- የሻወርና ሽንት ቤት ሥራ በሥፋት ቀጥሎ ለተጠቃሚዎች ገቢ ማግኛ ቢውል
- ህብረተሰቡ ፕሮጀክቱን በባለቤትንት ስሜት መደገፍ ቢጀምር
- ሁሉም በእኩል ጊዜ ጀምረው የተጠቃሚዎች የቆታ ጊዜ 5 ዓመት ቢሆን
- ኮታና ክፍያ ቢያድግ
- በአካባቢ ጥበቃ እና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ላሉ ላሉ የህብረተሰብ ክፍሎች የሥራ እድል የፈጠረ በመሆኑ በህብረተሰቡ ከፍተኛ ተቀባይነት ያሰገኘ በመሆኑ ቢቀጥል

**ማጠቀሻዎች**


1. CENCOSAD. (1994). *Community Health and Nutrition Assessment in Southern Ethiopia*. CENCOSAD Publications, Addis Ababa, Ethiopia.
2. Deelstra, T. 2000. “Urban Agriculture and Sustainable Cities.” In *Growing Cities, Growing Food: Urban Agriculture on the Policy Agenda*, edited by N. Bakker et al., 43—66. Feldafing: DSE.
3. FEDERAL URBAN JOB CREATION AND FOOD SECURITY AGENCY (2018). Public Work Guid Line
4. Klemsu, A. (2000). *Urban Poverty and Social Development in the Horn of Africa*. Horn Africa Press, Nairobi, Kenya.
5. MUDC( ). Social Protection Policy
6. MUDC(2020). Urban Productive Safety Net and Jobs Program (UPSNJP) Program Implementation Manual
7. MUDH (2015). Urban Food Secuirity Strategy
8. Smit, Barry, Ian Burton, R.J.T. Klein, and Richard Street. 1996. *Adaptation to Climate Change in the Context of Sustainable Development and Equity*. Ottawa: Environment Canada.
9. United Nations Development Programme (UNDP). 1996. *Human Development Report 1996*. New York: Oxford University Press.
10. United Nations Development Programme (UNDP). 1996. *Human Development Report 1996*. New York: Oxford University Press.
11. United Nations Development Programme (UNDP). 1996. *Human Development Report 1996: Economic Growth and Human Development*. New York: Oxford University Press.